


የኮሎምቢያ ድስትሪክት

# የተማሪ መንንዣ የቤተሰብ መመሪያ፡–

## 2023-24 የትምህርት ዓመት

የስቴት
ትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ ቢሮ

# ማውጫዎች


**3 እንኳን ወደ 2023-24 የትምህርት ዘመን በሰላም መጡ**

**4 ቤተሰቦች በአውቶቡስ ስለመጓጓዝ ምን ማወቅ አለባቸው?**

4 OSSE-DOT አውቶቡሶችን ለመንዳት ብቁ ሆነው ማነው?

4 ቤተሰቦች በትምህርት ዓመቱ ምን አይነት የዘመነ መረጃ መስጠት ይችላሉ?

5 በየቀኑ ጧት ጧት ቤተሰቦች ለመውሰድ ለመዘጋጀት ምን ማድረግ አለባቸው?

5 በየቀኑ ከትምህርት በኋላ ቤተሰቦች ለማድረስ ለመዘጋጀት ምን ማድረግ አለባቸው?

5 OSSE-DOT የመጓጓዣ አገልግሎት የሚሰጠው በየትኞቹ ቀናት ላይ ነው?

6 ተማሪዬ ለምን ያህል ግዜ ነው በአውቶቡስ ላይ የሚቆየው?

6 ተማሪዬ የደህንነት ጉዳይ ቢያጋጥመው ምን ማድረግ አለብኝ?

6 የOSSE መጥፎ የአየር ሁኔታ ፕሮቶኮል ምንድን ነው?

**7 የOSSE-DOT የተማሪዎቹ መጓጓዣን በተመለከተ ለሚኖሩኝ ጥያቄዎቹ ማንን ማነጋገር አለብኝ?**

7 የወላጅ መርጃ ማዕከል

7 እለታዊ የOSSE-DOT ዝማኔ ድህረገፅ

7 OSSE ትዊተር

**8 የመጓጓዣ አማራጮቹ**




# እንኳን

ወደ

# 2023-24 ትምህርት ዘመን በደህና መጡ

የግዛት ትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ ቢሮ፣ የተማሪ መጓጓዣ ክፍል (OSSE-DOT) ከትምህርት ቤት እና ወደ ትምህርት ቤት ብቁ ለሆኑ አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ደህንነቱ የተጠበቀ፣ የሚታመን እና ቀልጣፋ ትራንስፖርት ለማቅረብ ከቤተሰቦች እና ከትምህርት ቤቶች ጋር በትብብር ይሰራል።

# ቤተሰቦች በአውቶቡስ ስለመጓዝ ምን ማወቅ አለባቸው?

OSSE-DOT ብቁ ከሆነው ተማሪ መኖሪያ ቤት ወደ ቤት እና ከትምህርት ቤት ወደ መኖሪያ ቤት የትምህርት ቤት አውቶቡስ የመጓጓዣ አገልግሎቶችን ይሰጣል። ለOSSE-DOT የሚሰጥ የተማሪ አድራሻ የኮሎምቢያ ድስትሪክት ነዋሪነትን ለመጀመር ጥቅም ላይ ከዋለ አድራሻ ጋር መዛመድ አለበት።[1] OSSE-DOT ተማሪ የሚያጓጉዙ ተሽከርካሪዎን የሚነዱ ሹፌሮችን እና ተቆጣጣሪዎችን (“የአውቶቡስ ሰራተኞች”) ይቀጥራል። ተሽከርካሪው ደህንነቱ ተጠብቆ እንዲሰራ ሹፌሮች ሃላፊነት አለባቸው። የአውቶቡስ ተቆጣጣሪዎች ተማሪዎች ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ የማሳፈር፣ አዳዲስ መረጃዎችን የመስጠት እና ተማሪዎች ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ ከተሽከርካሪው እንዲወርዱ የመደገፍ ሃላፊነት አለባቸው። OSSE-DOT ተማሪዎች የትምህርት ቤት ደውል ከመደወሉ ከ10 እስከ 30 ደቂቃ በፊት እንዲደርሱ ያቅዳል። OSSE-DOT አንድ ተማሪ ወደ/ከአውቶቡስ ሲሸጋገር በተማሪው ለግል የተዘጋጀ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ላይ በመመስረት የተመረጡ አቅርቦቶችን  በመጠቀም ሊረዳ ይችላል፣ ለምሳሌ የተንቀሳቃሽ ወንበር አሳንሰር፣ መወጣጫዎችን፣ የእጅ በእጅ መደገፊየዎችን እና የመጓጓዣ ወንበሮች።

በአጠቃላይ፣ የአውቶቡስ ሰራተኞች የሚከተሉትን ማድረግ አይችሉም፡-

- በማንኛውም ሁኔታ የተማሪ መኖሪያ ቤት መግባት፤
- የአፓርታማ ህንፃዎች፣ መተላለፊያዎች፣ መግቢያ መንገዶች ወይም ጠባብ መንገዶች ውስጥ መግባት፣
- ትርፍ ሻንጣ፣ ተጨማሪ መሳሪያን ወይም መድሃኒቶችን ማጓጓዝ፣
- በአውቶቡስ ላይ ለተረሱት ዕቃዎች ሃላፊነት መውሰድ፤
- ተማሪን በአካል ማገድ ወይም መድሃኒት መስጠት፤
- ምግብ ወይም መጠጦችን ማቅረብ፤
- ከማንኛውም ሰው ስጦታ መቀበል፤
- ተንቀሳቃሽ ወንበር ወይም የደህንነት መሳያዎችን መጠገን፤
- የደህንነት ቀበቶዎችንና ማንጠልጠያ ጠባቂዎችን ማደል፤ እነዚህ በ IEP በተጠየቀው መሰረት በ OSSE የደህንነት ቡድን የሚታደሉ ናቸው::
- ተማሪዎችን ለማሳፈር ወይም ከባስ ለማውረድ(ድንገተኛ ሁኔታ ካልተፈጠረ በቀር) በአካል መውሰድ/ከፍ ማድረግ
- ዳይፖሮችን፣ የሚጣል ዳይፐር መቀየር ወይም ማልበስ፤
- ከሌሎች ጠባቂዎች ወይም ከውጪ ባለድርሻ አካላት ጋር የተማሪ መረጃ መጋራት፤
- ተማሪዎችን በአውቶቡስ ላይ ያለክትትል መተው፤
- ማንኛውንም ተማሪ ያልተፈቀደ ቦታ ላይ ማውረድ ወይም ትቶ መሄድ፤ ወይም
- ተማሪዎችን በማንኛውም ምክንያት መሸከም።

1 በተለዩ ሁኔታዎች ላይ ለሚገኙ ተማሪዎች አንድ በአንድ አቅርቦቶች ይዘጋጅላቸዋል።

## OSSE-DOT አውቶቡሶችን ለመንዳት ብቁ ሆነው ማነው?

OSSE-DOT ተማሪው የIEP ወይም ክፍል 504 እቅዱ ላይ ልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶችን ለማግኘት የመጓጓዣ አገልግሎቶች ማግኘት እንዳለባቸው ለሚገልጽ አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ብቻ በየቀኑ የመጓጓዣ አገልግሎቶችን ይሰጣል። OSSE-DOT ለመጓጓዣ ብቁ የሚሆነው ተማሪ ማን እንደሆነ አይወስንም። አካል ጉዳተኛ የሆነ ተማሪ ኖሮዎት አላግባብ የመጓጓዣ አገልግሎቶችን ተከልክያለው ብለው ካመኑ፣ እባክዎትን የተማሪዎትን ትምህርት ቤት ያግኙ።

## ቤተሰቦች በትምህርት ዓመቱ ምን አይነት የዘመነ መረጃ መስጠት ይችላሉ?

- እባክዎትን ለውጥ በሚኖርበት በማንኛውም ጊዜ ለትምህርት ቤትዎ የዘመነ የእውቂያ መረጃ፣ ፈቃድ ያለው መረጃ ተቀባይ እና የአደጋ ጊዜ የእውቂያ መረጃ ማቅረብዎን እርግጠኛ ይሁኑ።
    - የOSSE ስርዐት ይህን መረጃ የሚቀበለው ከተማሪው ትምህርት ቤት ብቻ ነው። ስርዐቱ ይህንን መረጃ በቀጥታ ከቤተሰብ አይቀበልም።
- ተማሪዎት በግማሽ የትምህርት ዓመቱ ለማጓጓዣ አገልግሎቶች ብቁ ከሆነና ተማሪዎ በአውቶቡስ እንዲሄድ ከፈለጉ፣ እባክዎ ትምህርት ቤትዎ የተማሪዎን የማጓጓዣ ጥያቄ ቅጽ ለOSSE ቶሎ እንዲያቀርብ ይጠይቁ።
- ተማሪዎ በማንኛውም ጊዜ የማጓጓዣ አገልግሎቱን መጠቀም ካቆመ፣ እባክዎን ለ ወላጅ መርጃ ማዕከል በ(202) 576-5000 ይደውሉ። ይህ OSSE-DOTን ቀልጣፋ የመጓጓዣ አገልግሎቶችን ለሚስያፈልጓቸው ተማሪዎች እንዲሰጥ ይረዳዋል።
    - አንድ ተማሪ ለአምስት ተከታታይ የትምህርት ቀናት በአውቶቡሱ ካልተጓዘ፣ የልዩ የትምህርት መጓጓዣው በOSSE-DOT ሊቋረጥ ይችላል፤ ትምህርት ቤቶቹም አስቀድመው እንደያውቁትና ከወላጆች/አሳዳጊዎች ጋር ተገናኝተው ለቀረው ተሳፋሪ ተማሪ ችግሮች መፍትሄ ለመስጠት ሃላፊነት ይወስዳሉ።

## ቤተሰቦች በእያንዳንዱ ማለዳ ለመውሰድ ለመዘጋጀት ሊያደርግ የሚገባው ምንድነው?

OSSE-DOT ለእያንዳንዱ ቤተሰብ የታቀደውን የመውሰጃ ጊዜ የሚሰጥ ይሆናል። OSSE-DOT መንገዶችን ስለሚያስተካክል ይህ ጊዜ በአመቱ ውስጥ ሊቀየር እንደሚችል እባክዎ ያስታውሱ። ቤተሰቦች ከታቀደው ጊዜ 15 ደቂቃ በፊት ወይም በኋላ ተማሪዎቻቸውን ለመውሰድ ሊዘጋጁ ይገባል። ለምሳሌ፣ የተማሪዎ የመውሰጃ ጊዜ 8 a.m. ከሆነ፣ ተማሪው ውጪ ሊገኝ እና ከ7:45 a.m. እስከ 8:15 a.m. ወደ አውቶቡሱ ለመግባት ዝግጁ ሊሆን ይገባል። ተማሪዎች ከመኖሪያ ቤትዎ የውጪኛው በር ላይ የሚወሰዱ ይሆናል። እባክዎ በአየር ሁኔታ፣ በትራፊክ ሁኔታዎች እና በሌሎች ያልተጠበቁ ሁኔታዎች ምክንያት መዘግየቶች ሊከሰቱ እንደሚችሉ ያስታውሱ። እባክዎ osse.dc.gov/page/daily-dot-updates ይጎብኙ ወይም ተማሪዎ(ዎች) መንገዳቸው ላይ መዘግየት አጋጥሟቸው እንደሆነ ለማወቅ ለወላጅ መርጃ ማዕከል በ(202) 576-5000 ይደውሉ።

## ከትምህርት በኋላ ለማድረስ ለመዘጋጀት ቤተሰቦች ምን ሊያደርጉ ይገባል?

አንድ ተማሪ "ራሱን የቻለ ተማሪ ማድረስ" ለሚባለው በትክክል ፈቃድ ካልተሰጠው በስተቀር፣ ፈቃድ ያለው ተቀባይ በተዘጋጀው የከሰአት ማድረሻ አድራሻ መገኘት አለበት። ስለዚህ፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች ለማድረስ በየቀኑ ፈቃድ ያለው ተቀባይ መዘጋጀቱን ማረጋገጥ አለባቸው። OSSE-DOT መንገድ ላይ ድንገተኛ አደጋዎች ሊኖሩ እንደሚችሉ ይገነዘባል እና ወላጆች ተማሪያቸውን አደጋ ወይም ድንገተኛ አደጋ ከተከሰተበት ቦታ ለመውሰድ ሊመርጡ ይችላሉ። ብዙ ቤተሰቦች ከመንገዱ ላይ ሌሎች ተማሪዎችን ለማጓጓዝ በሚፈልጉባቸው ሁኔታዎች፣ እባክዎን የሚፈለገው ተቀባይ የመጓጓዣ አገልግሎቶች ለሚያገኙ ለእያንዳንዱ ተማሪ ፈቃድ ማግኘቱን ያረጋግጡ። መረጃውን ለአካባቢዎ የትምህርት ድርጅት (LEA) በመላክ ፈቃድ ያለው ተቀባይ ተመስርቷል። ፈቃድ ያላቸውን ተቀባዮች ዝርዝርዎን ወደ ተማሪዎ ፋይል ለማከል የመጓጓዣ ጥያቄ ቅጽን የሚሞሉ ይሆናል።

እድሜያቸው ከ12 በላይ የሆኑ እና በIEP እና 504 እቅዳቸው ላይ "ልዩ ፕሮግራም ማግኘት" በሚለው የመጓጓዣ ክፍል ብቁ የሆኑ ተማሪዎች ብቻ ራሱን የቻለ ተማሪ ማድረስ በሚለው ስር ሊመደቡ ይችላሉ። ተማሪዎን "ራሱን የቻለ ተማሪ ማድረስ" በሚለው ስር ተማሪዎን ለመመደብ፣ እባክዎን የፈቃድ ቅጽ ሞልተው ለትምህርት ቤትዎ ያስገቡ።

OSSE-DOT ስልጣን ያለው ተቀባይ ማግኘት ካልቻለ፣ የአውቶቡሱ ሹፌር ተማሪውን ወደ ዲሲ የልጅ እና የቤተሰብ አገልግሎቶች ድርጅት (CFSA) ማድረስ አለበት። CFSA ለተማሪው አስተማማኝ የሆነ አካባቢ ለማቅረብ ፕሮቶኮሎችን የሚከተል ይሆናል። የተማሪው ቤተሰብ ተማሪውን በ200 I St. SE, Washington, DC 20003 ከሚገኘው CFSA የመውሰድ ሃላፊነት ይኖርበታል። ወላጆች/አሳዳጊዎች የልጅ ክትትልን እና መልቀቅን በሚመለከት በፖሊሲዎቻቸው እን አሰራሮቻቸው ላይ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት CFSA ለማነጋገር በ(202) 442-6100 ሊደውሉ ይገባል።

## OSSE-DOT የመጓጓዣ አገልግሎቶችን የሚሰጠው በምን ቀናት ነው?

OSSE-DOT ብቁ ለሆኑ ተማሪዎች ለትምህርት አመት ቆይታ እና ለተራዘመ የትምህርት አመት አገልግሎቶች የመጓጓዣ አገልግሎት ይሰጣል። ይሁን እንጂ፣ OSSE-DOT ለ2023-24 የትምህርት አመት በሚከተሉት የዲሲ መንግስት ህጋዊ በአላት ላይ ተማሪዎችን አያጓጉዙም (ከታች ተዘርዝረዋል)። የተማሪዎ ትምህርት ቤት በእነዚህ የበአል ቀናት ክፍት የሚሆን ከሆነ፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች በosse.dc.gov/node/719832 ላይ ለሚገኘው የግል መጓጓዣ ቅጽ ጥያቄ በማስገባት ተማሪዎቻቸውን በራሳቸው ለሚጓጓዙበት የማካካሻ ክፍያ ሊያገኙ ይችላሉ።

- **የስራ ቀን፡**– ሰኞ፣ ሴፕቴምበር 4፣ 2023
- **የሃገር ተወላጅ ህዝቦች ቀን፡**– ሰኞ፣ ኦክቶበር 9፣ 2023
- **የአርበኞች ቀን፡**– አርብ፣ ኖቬምበር 10፣ 2023
- **የምስጋና ቀን፡**– ሃሙስ፣ ኖቬምበር 23፣ 2023
- **የገና ቀን፡**– ሰኞ፣ ዲሴምበር 25፣ 2023
- **የአዲስ አመት ቀን፡**– ሰኞ፣ ጃንዋሪ 1፣ 2024
- **የዶ/ር ማርቲን ሉተር ኪንግ ልደት፡**– ሰኞ፣ ጃንዋሪ 15፣ 2024
- **የዋሽንግተን ልደት፡**– ሰኞ፣ ፌብሩዋር 19፣ 2024
- **የዲሲ ነጻነት ቀን፡**– ማክሰኞ፣ ኤፕሪል 16 2024
- **የመታሰቢያ ቀን፡**– ሰኞ፣ ሜይ 27፣ 2024
- **የጁን አስራ ዘጠኛ ብሄራዊ ነጻነት ቀን፡**– ረቡዕ፣ ጁን 19፣ 2024
- **የነጻነት ቀን፡**– ሃሙስ፣ ጁላይ 4፣ 2024



## ተማሪዬ ለምን ያህል ግዜ ነው በአውቶቡስ ላይ የሚቆየው?

የተማሪው የሚጠበቀው የጉዞ ጊዜ የትምህርት ቤት ትምህርት ጊዜ፣ በእያንዳንዱ አውቶቡስ ላይ ያሉ ተማሪዎች ብዛት፣ የመኖሪያ ቦታ፣ ከትምህርት ቤት ያለውን ርቀት እና በመንገዱ ላይ እያንዳንዱን ተማሪ ለመጫ የሚወስደውን ጊዜ ጨምሮ በተለያዩ ምክንያቶች ላይ የተመሰረተ ነው። ወደ አውቶቡሱ በእግር የሚሄዱ ተማሪዎችን ለመጫን/ለመውረድ ሶስት ደቂቃ ተሰጥቷቸዋል። ተንቀሳቃሽ ወንበር ተጠቃሚ ተማሪዎች በእያንዳንዱ ፌርማታ ለመጫን/ለማውረድ አምስት ደቂቃ ተሰጥቷቸዋል። እንዲሁም የትራፊክ እና የአየር ንብረት ሁኔታዎች በጉዞ ጊዜ ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ። በትምህርት አመቱ፣ OSSE-DOT መንገዶችን እንደ አስፈላጊነቱ ይቆጣጠራል እንዲሁም ያስተካክላል።




### በፕሮግራም መገኛ መሰረት፣ ጉዞው የሚወስደው ጊዜ በግምት...

- በዲሲ ውስጥ (90 ደቂቃ)
- ከዲሲ በ6 ማይል ላይ (105 ደቂቃ)
- ከዲሲ በ6 እስከ 15 ማይል ሲሆን (120 ደቂቃ)
- ከዲሲ ከ15 ማይል በላይ ሲሆን (190 ደቂቃ)

## ተማሪዬ የደህንነት ጉዳይ ቢያጋጥመው ምን ማድረግ አለብኝ?

ለOSSE-DOT በጣም አሳሳቢው ጉዳይ የተማሪ ደህንነት ነው።[2] አውቶቡሱ በጉዞ ላይ በሚሆንበት ጊዜ የትምህርት ቤት የአውቶቡስ ቡድን ለድንገተኛ አደጋ ዝግጁ እንዲሆን OSSE-DOT አሽከርካሪዎች እና ረዳቶችን በመጀመሪያ ደረጃ የህክምና እርዳታ እና በCPR በማሰልጠን የተማሪ ደህንነትን ከፍ ያደርጋል። ድንገተኛ አደጋ በሚፈጠርበት ጊዜ፣ አሽከርካሪዎች እና ረዳቶች በመጀመሪያ የተማሪዎቹን ደህንነት የሚከታተሉ ሲሆን ከዚያም የድንገተኛ አደጋ ሰራተኞችን (911) ያነጋግራሉ።

በOSSE-DOT ሰራተኛ ወይም በሌላ ተማሪ ምክንያት ወደ/ከ ትምህርት ቤት በሚጓዙበት ጊዜ ተማሪዎ የተማሪ ደህንነት ችግር ካጋጠመው፣ እባክዎ ክስተቱን ሪፖርት ለማድረግ የወላጅ መርጃ ማዕከልን በ(202) 576-5000 ያነጋግሩ። አንድ ጊዜ ሪፖርት ከተደረገ በኋላ፣ OSSE ለችግሩ መፍትሄ ለመስጠት ምርመራ የሚያደርግ ሲሆን እንደ ተገቢነቱ በሰራተኛው ላይ ቅጣት ያወጣል።

ተገቢ በሆነ የመስተንግዶ እጥረት ምክንያት የደህንነት ክስተት እንደተፈጠረ ካመኑ (ለምሳሌ፣ የመወጣጫ አለመኖር)፣ በአውቶቡሱ ላይ በOSSE-DOT የሚቀርበው መስተንግዶ የሚወሰነው በIEP ሂደት እና በሰነድ መሰረት ስለሆነ እባክዎ የትምህርት ቤትዎን የIEP ቡድን ያነጋግሩ።

2 መጓጓዣ OSSE-DOT በእንክብካቤያችን ውስጥ ያለውን የእያንዳንዱን ተማሪ ደህንነት ለመጠበቅ ሊኖረው በሚችል አቅም ላይ በመመስረት የሚቀርብ ተዛማጅ አገልግሎት ነው።

## የOSSE መጥፎ የአየር ንብረት ፕሮቶኮል ምንድን ነው?

OSSE-DOT በመጥፎ የአየር ንብረት ወቅት የሚከተሉትን የአገልግሎት ደንቦች ይጠቀማል።

- **CODE RED (ኮድ ሬድ):**– መጓጓዣ የለም
- **CODE YELLOW (ኮድ የሎው):**– የተገደበ መጓጓዣ
- **CODE GREEN (ኮድ ግሪን):**– ሙሉ በሙሉ የሚሰራ

የመጥፎ የአየር ንብረት ደንቦች እና የአሰራር ሂደቶች በosse.dc.gov/page/student-transportation-inclement-weather-plan ላይ ተለጥፈዋል። OSSE-DOT በመጥፎ የአየር ንብረት ምክንያት አገልግሎት በማይሰጥበት ጊዜ የተማሪያቸው ትምህርት ቤት ክፍት የሚሆን ከሆነ ቤተሰቦች አማራጭ መጓጓዣ የማዘጋጀት ሃላፊነት አለባቸው። በ Code Yellow ሁኔታዎች፣ እባክዎን osse.dc.gov/page/daily-dot-updates ይጎብኙ ወይም የተማሪዎን መንገድ በሚመለከት መረጃ ለማግኘት ለወላጅ መርጃ ማዕከል በ(202) 576-5000 ይደውሉ።

# የ OSSE-DOT የተማሪ መጓጓዣን በተመለከተ ማነጋገር የሚገባኝ ማንን ነው?

## የቤተሰብ መርጃ ማዕከል

የቤተሰብ መርጃ ማዕከል(PRC) በOSSE-DOT፣ በቤተሰብ እና ትምህርት ቤቶች መካከል እንደ ቀዳሚ የመገናኛ ድልድይ ያገለግላል። PRCን ከሰኞ እስከ አርብ በ(202) 576-5000 ከ5 a.m. እስከ 7 p.m. ማግኘት ይችላሉ። PRC በድምጽ እና በጽሁፍ መልዕክቶች መልዕክት በመለዋወጥ ጥሪት ያለው የደንበኛ አገልግሎት ይሰጣል እንዲሁም ለተማሪው የመጓጓዣ ጉዳዮች መፍትሄ ይሰጣል።

- ለትምህርት አመቱ ልዩ የመንገድ መረጃ።
- የመንገድ ለውጦች።
- የመጨረሻ እና ቀዳሚ መንገዶች።
- መጥፎ የአየር ንብረት መዘግየቶች እና/ወይም ስረዛዎች።

የጽሁፍ መልዕክቶችን ጨምሮ ከOSSE-DOT መረጃ መቀበልዎን ለማረጋገጥ የእውቂያ መረጃን ከተማሪዎ ትምህርት ቤት ጋር ማዘመን መቀጠል ወሳኝ ነው። በትምህርት አመቱ መጀመሪያ እና በአስቸጋሪ የአየር ንብረት ወቅት እባክዎ ከአማካይ የመጠበቂያ ጊዜ በላይ ሊቆዩ እንደሚችሉ ያስቡ። ለትዕግስትዎ አሰቀድመን እናመሰግናለን።

የወላጅ መርጃ ማዕከል የሚከተሉትን አገልግሎቶች ይሰጣል፦

- **የአውቶቡስ ሁኔታ መረጃ:**– የPRC ተወካይ የሚገመተውን ወደ ትምህርት ቤት እና/ወይም ወደ ቤት መድረሻ ሰዓት ለመወሰን ተማሪው የተሳፈረውን አውቶቡስ መከታተል ይችላል።
- **ቅሬታዎችን መቀበል እና መከታተል :**– በ10 ቀናት ውስጥ ከሶስት ተከታታይ የመጓጓዣ ገጠመኞች በኋላ፣ ፈቃድ ያለው ሰው የPRC ተወካይ ቅሬታ እንዲያስገባ ሊጠይቅ ይችላል።
- **የመንገድ መዛባት ጥያቄ:**– በማንኛውም ከታቀደው መነሻ ሰዓት በፊት፣ ፈቃድ ያለው ግለሰብ የPRC ተወካይ የጠዋት እና/ወይም የከሰዓት የመጓጓዣ አገልግሎትን ለተወሰነ ቀን እንዲሰረዝ ጥያቄ እንዲያቀርብ ሊጠየቅ ይችላል።
- **የመንገድ ማረጋገጫ:**– የPRC ተወካይ የመንገዱን ቁጥር፣ የመሳፈሪያና የማውረጃ ሰዓታትን ፈቃድ ላለው ግለሰብ(ቦች) ማረጋገጥ ይችላል።
- **የመንገድ ቅያሬ ማሳታወቂያ:**– የPRC ተወካይ ከታቀደው የመንገድ መጀመሪያ ቀን ቢያንስ 48 ሰአታት ቀደም ብሎ የመንገድ ለውጦች ማስታወቂያዎችን ይሰጣል (ማለትም የመውሰጃ እና የማውረጃ ሰአታት፣ የመንገዱን ቁጥር ቅያሪ)።
- **የመንገድ መዘግየት ማሳታወቂያ:**– መንገዱ ከታቀደው መድረሻ ሰዓት 30 ደቂቃ ከቀደመ ወይም ከዘገየ PRC የስልክና የፅሑፍ መልዕክት ለቤተሰቦች ይልካል።

በPRC ጥቅም ላይ የሚውሉ መረጃዎች በሙሉ ለOSSE በተማሪው LEA የሚቀርቡ ናቸው። በመሆኑም፣ PRC የእውቂያ ዝርዝር አድራሻዎችን፣ የመኖሪያ መረጃን ወይም የመንገድ ዝርዝሮችን ጨምሮ ነገር ግን በእነዚህ ሳይወሰን፣ ማንኛውንም መረጃ ማዘመን፣ መጨመር፣ መለወጥ፣ አይችልም። የተማሪውን መረጃ ማዘመን ካስፈለገ፣ እባክዎ የተማሪውን ትምህርት ቤት/ LEA አስተባባሪ ያነጋግሩ።

### በተለምዶ የሚጠየቁ ጥያቄዎች፦

**ትምህርት ከመጀመሩ በፊት PRC ቤተሰቡን የሚያገኘው ከምን ያህል ቀናት ቀደም ብሎ ነው?** የጉዞው ቀን ከሚጀምርበት የታቀደው ቀን በፊት ቢያንስ 48 ሰዓታት ቀደም ብሎ።

**የመገናኛ ዘዴዎች ምንድን ናቸው?**
የፅሁፍ መልዕክት ስርዐታችን ለቤተሰቦች ስለጉዞው ሁኔታ መረጃ ለመላክ ይጠቅማል። ቤተሰብ ባቀረበው የቤት ስልክ ቁጥር ወይም የእጅ ስልክ ቁጥር ላይ በመመስረት፣ የመንገድ ሁኔታውን በሚመለከት መረጃ የያዘ የፅሑፍ መልዕክት ወይም የድምፅ ጥሪ ይደርሳቸዋል።

**በጉዞ መረጃ ዝማኔዎችን በኢሜይል መላክ ይቻላል?**
OSSE ከLEAዎች የቤተሰብን ኢ-ሜይል አይቀበልም። በመሆኑም፣ በአሁኑ ወቅት የመልዕክት መላኪያ ስርዓታችን በፅሁፍ መልዕክት እና በድምጽ ጥሪዎች ብቻ የተወሰነ ነው።

***PRC* የተማሪዬን መረጃ ማዘመን የማይችለው ለምንድነው? (ለምሳሌ የቤት አድራሻ ለውጦች፣ የወላጅ ስልክ ቁጥር፣ ወዘተ)** OSSE-DOT እና LEAዎች የተማሪ መረጃ በእያንዳንዱ የመንግስት ተቋሞች ዘንድ ትክክለኛ እና የዘመነ መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው። በመሆኑም፣ ሁሉም የተማሪ መረጃ በLEAs ተጠብቆ የሚቆይና ለውጥ ሲኖር ለOSSE በየቀኑ ይቀርባል።

## እለታዊ የOSSE-DOT ዝማኔ ድህረገፅ

ቤተሰቦች ላቀረቧቸው ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት፣ በ2023፣ OSSE-DOT የተማሪያቸውን (ዎች) የአውቶቡስ(ሶች) የጊዜ ሁኔታ በሚመለከት ለቤተሰቦች እለታዊ መረጃ የሚሰጥ ለህዝብ ተደራሽ የሆነ ድህረገፅ ፈጥሯል። የተማሪውን ግላዊነት ለመጠበቅ፣ OSSE-DOT እያንዳንዱ አውቶቡስ መቼ በእያንዳንዱ ተማሪው ቤት እንደሚርስዝርዝር አያስቀምጥም። ይልቁንም፣ ድህረገፁ የእያንዳንዱን አውቶቡስ የመነሻ ሰዓት ለቤተሰብ ያሳውቃል። በጉዞ ላይ መንገድ ላይ በሚያጋጥሙ ሁኔታዎች ምክንያት አውቶቡሱ ተጨማሪ ጊዜ ሊወስድ ወይም ያልተጠበቀ መዘግየት ሲያጋጥመው የሰአት መነሻ ቤተሰቦች የጠዋት የመጓጓዣ ውሳኔዎችን እንዲወስኑ በአጠቃላይ አስተማማኝ የሆነ ጠቋሚ መረጃ ይሰጣል። ቢያንስ በየቀኑ የሚዘምነው ድረገጽ፣ የትኛው አውቶቡስ "እንደዘገየ" "እንደተበላሸ" ወይም "አገልግሎት እንደማይሰጥ" ያሳያል።

- **የዘገየ ጉዞ:**– ዋስትና ያለው ሽፋን ነው ነገር ግን ተማሪዎች ሲሳፈሩም እና/ወይም ሲወርዱ መዘግየት (እስከ 90 ደቂቃ ድረስ) ያጋጥማቸዋል።
- **የተበላሸ መንገድ:**– በሰራተኞች እጥረት ተግዳሮቶች ምክንያት፣ OSSE-DOT አንድ አሽከርካሪ አንዱን ጉዞ ሲጨርስ ሌላ መንገድ ላይ ለመመደብ እየሞከረ ነው። በመንገዱ ላይ ያሉ ተማሪዎች የአገልግሎት መዘግየት ያጋጥማቸዋል።
- **አገልግሎት የለም:**– OSSE-DOT መንገዱን ማገልገል አልቻለም።

## OSSE ትዊተር

OSSE-DOT ዕለታዊ ዝማኔዎችን፣ መጥፎ የአየር ሁኔታን ማስታወቂያዎችን እና ሌሎች ወቅታዊ ዝማኔዎችን በOSSE የትዊተር መለያው ላይ ያጋራል።

# የመጓጓዣ አማራጮች

OSSE-DOT ደህንነቱ የተጠበቀ ፣አስተማማኝ እና ቀልጣፋው መጓጓዣን ብቁ ለሆኑ የዲስትሪክት ተማሪዎች የማቅረብ ሃላፊነቱን ለማሳካት የተለያዩ ዘዴዎችን እና አማራጮችን መጠቀም ወሳኝ ነው፡፡

## የቤተሰብ መጓጓዣ ማካካሻ ፕሮግራም

OSSE DOT በብቁ የሆኑ አካልጉዳተኛ ተማሪዎችን ወደ እና ከትምህርት ቤት ለሚያጓጉዙ ወላጆችንና አሳዳጊዎች ካሳ ይከፍላል፡፡ ከቤተሰብ መጓጓዣ የካሳ ፕሮግራም ጋር በተያያዘ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት እባክዎ QR ኮዱን ይቃኙ፡፡

## Kids Ride Free (የህፃናት ነፃ ጉዞ) ፕሮግራም

የKids Ride Free (ህፃናት ነፃ ጉዞ) ፕሮግራም ተማሪዎች በዲስትሪክቱ ውስጥ ባሉ በሜትሮባስ፣ በዲሲ ሰርኩሌተር እና ሜትሮሬይል ለትምህርት ቤት እና ከትምህርት ቤት ጋር ለተገናኙ ተግባራት በነፃ እንዲጓዙ ይፈቅድላቸዋል፡፡ ስለዚህ ፕሮግራም እና ብቁነት የበለጠ ለማወቅ እባክዎ QR ኮዱን ይቃኙ፡፡

## አማራጭ የመጓዣ አቅራቢዎች

OSSE-DOT በዲሲ መንግስት የውሎች እና አቅርቦት በኩል ከተለያዩ የመጓጓዣ አቅራቢዎች ጋር ይዋዋላል፡፡ ተማሪዎች በOSSE-DOT ውሳኔ ለአማራጭ አቅራቢዎች ይመደባሉ፡፡ ተማሪዎ ለአቅራቢ ተመድቦ ከሆነ ፣ OSSE-DOT የመሳፈሪያ እና ማውረጃ ሰዓታትን፣ የአቅራቢውን ኩባንያ ስም፣ የተሽከርካሪውን አይነት እና ቀለም በተመከተ ማስታወቂያ ይልክሎታል፡፡

የግዛት ትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ ቢሮ

1050 First Street, NE, Washington, DC 20002